# የወያኔው ጠ/ሚ፤ የውጭ ጉዳይ ሚንስትርና ፕሬዘዳንቱ በበረራ ላይ

ጠቅላይ ምኒስትራችን ፕሬዘዳታችንና የውጭ ጉዳይ ሚንስትራችን በአውሮፕላን ሲጓዙ አውሮፕላኑ በሽብርተኞች ይጠለፋል። በዚህ ግዜ ጠቅላይ ሚንስትሩና የውጭ ጉዳይ ሚንስትሩ ማንነታቸው እንዳይታወቅ ቶሎ ብለው የፓይለቶቹን ልብስ ለብሰው ከፓይለቶቹ ጋ ቦታ ይቀያየራሉ። ከጠላፊዎቹ አንዱ ወደ ኮክፒቱ በመሄድ የዋና ፓይለቱን ቦታ የያዙትን ጠቅላይ ምኒስትር አውሮፕላኑን ወደ ምናዝህ አቅጣጫ ካላበረርክ አንገልህን እበታትነዋለሁ ይላቸዋል።

እሳቸውም እኔን ከገደልክ ሁላችንም አብረን እንሞታለን ስለዚህ ያሰብከው አይፈጸምም ሲሉት ጠላፊው እንደገና ወደ ረዳት ፓይለቱ ይዞርና እንደዚያው ሲላቸው ስዩም መስፍንም ልክ እንደ ጠ/ሚንስትሩ እኔንም ከገደልከኝ ፓይለቱ ብቻውን ማብረር ስለማይችል አብረን ማለቅ ነው ብለው ያስፈራሩታል ።

አሁን ጠላፊው ዞር ሲል ከተሳፋሪው መሃል ፕሬዘዳንታችንን ያያቸውና እንዲያውም ዋናው ተገኘ የኢትዮጵያ ፕሬዘዳንት አይደሉ እርስዎ ኑ ወደዚህ ይልና ሽጉጡን አናታቸው ላይ ደግኖ ወደ ፓይለቶቹ በመሄድ የምላችሁን ካላደረጋችሁ የፕሬዘዳንታችሁን አንገል በዚህ ጥይት እበታትነዋለሁ ብሎ ሲደነፋ ሁለቱም ፓይለቶች ባንድ ድምጽ አንጎል ካለው በታትነው ! ብለው እርፍ